# <u>የአንድነት ፖለቲካዊ አቅጣጫ</u>

ባለፈው የቅዱስ ሚካኤል ክብረ ባህልን ያከበርኩት ቦስተን በሚገኘው ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ነበር። እና በክብረ ባህሉ ላይ ትምህርተ ቡራኬ ይሰጡ የነበሩት ስማቸውን በውል የማላስታውሰው ቀሲስ ነበሩ። ቀሲሱም የማስተማር ፀጋቸው እጅግ የተለየ ነበር። እና እኔም አጋጣሚውን በመጠቀም ከቀሲሱ አንደበት እየተዥጎደጎደ የሚወጣውን ማራኪ ቃላቶች በተመስጥኦ እከታተል ነበር።

በዚህን ወቅት ቀሲሱ ሁሌም ጥያቄ የሚሆንብኝን ነገር አንስተው ባማረ አንደበታቸው ሲያስተምሩ የተለየ ትኩረት በመስጠት እከታተል ነበር። እዬ በተለየ ተመስጥኦ እከታተለው የነበረው ትምህርት ኢትዮጵያ አገራችን ከገባችበት ውስብስብ ችግር ሊያወጣት የሚችል ጠቃሚ ነገርን የያዘ መልዕክት ነበር። መልእክቱንም! “ በአለም ላይ ሀያ አራት ሰአት ለእግዚአብሄር አምላክ ጸሎተ ልመናን በማቅረብ ኢትዮጵያውያኖችን የሚወዳደር እንደሌለ፤ ነገር ግን እያ ሁሉ ፀሎት አንዱም ወደ እግዚአብሄር ዳጃፍ እንደማይደርስ” ነበር ሲያስተላልፉ የነበረው።

ቀሲሱ ለዛ ማብራሪያ ሲሰጡም፤ “እግዚአብሄር አምላክ የፍጥሮቹን ጸሎት ሊቀበል የሚችለው እያ ፀሎት አቅራቢው ፍጡር ወደ ፀሎት ከመሄዱ በፊት ልቡን ለይቅርታና ለፍቅር አዘጋጅቶ ሲሄድ ብቻ እንደሆነ ነው።” እና እንደሳቸው አባባል የእኛ የኢትዮጵያኖች ጸሎት ከአምላክ አጠገብ መቅረብ አቅቶት ጸሎቱ በአየር ላይ ተንሳፎ ሊቀር የቻለው እና የህዝባችንም የእለት ተእለት ኑሮ እያሽቆለቆለ ሊመጣ የቻለው ልባችንን ለይቅርታና ለፍቅር ማዘጋጀት ተስኖን በመቅረቱ እንደሆነ ነው። መቼም በዛን ወቅት እድሉን አግኝቶ መልእከታዊ የሆነውን ትምህርት የተከታተለ ሰው እና በነገሩ አዎንታዊነት የተረታ ሰው ከራሱ ጋ ለመታረቅ ግብ ግብ ለመፍጠሩ ሳይታለም የተፈታ ነው።

እና እኔም በዛን ወቅት ከቀሲሱ ባገኙሁት አዎንታዊነትን ካዘሉ አባባሎች በመነሳት፤ ከብዙ የአእምሮ ክርክር በሁዋላ አንዳንድ ከበድ ላሉ ነገሮችም ይቅርታ መስጠት እንዳለብኝ በግሌ ተረድቼያለሁኝ። አገራችንም የገባችበትን ውስብስብ ችግር ከግምት በማስገባት ለምወዳት አገሬ ስል ይቅር ለእግዚአብሄር የመባባሉን መንገድ መርጬያለሁኝ።

እዬ የቀሲሱን መንገድ አመላካች ትምህርት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በመጥፋት ላይ ያለችውን አገሩን ለማዳን ሲል የመንፈሳዊውን ቃልም የግድ መቀበል እንዳለበት ይሰማኛል። እንግዲህ ለሁላችንም እንደሚገባን መንፈሳዊ ይዘቱ ይህንን ይመስላል። በእርግጥ ፖለቲካዊ ይዘትም የመንፈሳዊውን አመላካች መንገዶች በተወሰነ ደረጃ ይጋራል። እያማ ባይሆን ኖሮ በፖለቲካው ውስጥ ሕግና ደንቦችም ባልኖሩ ነበር። የመንፈሳዊ መፅሀፉም እንደሚያስረዳን ሰዎች የራሳቸውን ህግና ደንብ ቀርፀው በቀረጹት ህግና ደንብ መተዳደር እንዳለባቸው ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ በዚህ አጋጣሚ ሳልገልፅ የማላልፈው ነገር ቢኖር፤ ከበስተቷላ ብረዳውም አንድነት በህግና ደንቡ ውስጥ እንዳካተተው አንድ ሰው በስልጣን ዘመኑ ውስጥ ሕዝብን በድሎ ከነበረ ነገር ግን እራሱን በስልጣን ዘመኑ ያገለግለው ከነበረው መንግስት ለይቶ እንዲሁም የበደለውንም ሕዝብ ልባዊ ይቅርታ ጠይቆ እና ተፀፅቶ ከተገኘ ጉዳዩን የሚመለከታቸው ኮሚቴዎችም ተወያይተውበት ይቅርታውን ካፀደቁ ድርጅቱ እንደሚቀበል ከድርጅቱ ከፍተኛ ሰዎች ተረድቼያለሁኝ። በዚህ አጋጣሚ ከድርጅቱ አመራሮች ጋር በተፈጠረው ቅራኔ ከድርጅቱ ከተገለሉት ከመርህ ይከበር ሰዎችም እውነታው እያ እንደሆነ ነው የተገለጸው። ነገር ግን የመርህ ይከበር ሰዎች እንዳስረዱት ከሆነ ይቅርታ አጠያየቁ ልባዊ ካልሆነ ፓርቲው እንደማያስተናግድም አያይዘው ገልጸዋል።

***በሰሞኑ አነጋጋሪ አጀንዳ ወደነበረው የአቶ ስዬ አብርሀ እና የዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ጉዳይ ልምጣና እኔም የተሰማኝን ነገር አንዳንድ ልበል።***

እንደ እውነቱ ከሆነ ነገሮችን ከመረዳቴ በፊት የአቶ ስዬ አብርሀን እና የዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ወደ አንድነት የመቀላቀልን ዜና ስሰማ እጅግ ከተቃወምኩኝ ሰዎች አንዱ ነኝ። ምክንያቱም ወደዛ አይነቱ አመለካከት እንዳመራ ያደረጉኝ ነገሮች ቢኖሩ እነኝህ ሁለት ሰዎች በስልጣን ዘመናቸው ውስጥ በህዝብ ላይ አድርሰውት በነበረው የወንጀል ክብደት የተነሳ ነው። ነገር ግን ሰው በተፈጥሮው ስህተት ሳይሰራ መኖር እንደማይችል በውል የተረዱት የአንድነት አመራሮች በእንደዚህ አይነት ችግር ውስጥ ላለ ሰው ህግና ደንብን አርቅቀው ከስህተቱ ሊፀፀት የሚችልበትን መንገድ አዘጋጅተውለት ወደነሱ መንገድ እንዲመጣ ማድረጋቸው እጅግ የሚያስመሰግናቸው ጉዳይ ነው።

ከላይ የቀሲሱን አባባል በግሌ እንደተረጎምኩት ይቅር መባባል ወደፊት ከምናልመው ግብ ሊያደርሰን እንደሚችል እና በጥቂት ጸሎት ብቻ እንኳን አምላክ ለፀሎታችን ምላሹን በፍጥነት ሊሰጠን ይችላል በሚል ነው። እና አንድነቶችም የመንፈሳዊውን ቃል ጠቀሜታ ተገንዝበው የኢትዮጵያውያኖችን አንድነት ሊያጠናክር ከሚችለው ድምዳሜ ላይ መድረሳቸው ይበል የሚያሰኝ ነው።

ነገር ግን ቅሉ ለእኔ ያልተዋጠልኝ ነገር ቢኖር አሁንም አቶ ስዬ አብርሀ ይቅርታ የጠየቁበትን መድረክ እስካሁን ፈልጌ አለማግኘቴ ነው። በእርግጥ ለአንድነት ሰዎች እያን አይነቱን ነገር ከልባቸው ተፀፅተውበት ይቅር በሉኝ ብለዋቸው ይሆናል እኛ ባናውቅም። ነገር ግን ለአቶ ስዬ የምመክራቸው ነገር ቢኖር የደጋፊዎችን ውዥንብር ለማጥራትም ሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ ልባዊ ይቅርታ እንዲያገኙ ከፈለጉ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታን እንደተማጸኑት እሳቸውም ሊያደርጉት ይገባቸዋል። በዚህ አጋጣሚ አቶ ስዬ መረዳት ያለባቸው ነገር ቢኖር ሕዝብ ይቅርታ ካደረገ ይቅርታው ዘላለማዊ ሊሆን እንደሚችል ነው። ከአእምሮ ወቀሳም መዳን ይቻላል። ብቻ ለሁሉም ስህተትን አምኖ ይቅርታን መጠየቅ አዋቂነት እንጂ ሽንፈት አይደለም።

*የሆነው ሆኖ የይቅርታ አሰጣጡ ደንብ በአንድነት መርህዎ ውስጥ እስካለ ድረስ የአንድነት ደጋፊዎች የነአቶ ስዬን ወደ አንድነት መግባት መቃወሙ ሚዛን የሚደፋ አይሆንም። ምክንያቱም የአንድነት ደጋፊዎች የሚደግፉት ቃሉን **አንድነት** የሚለውን ሳይሆን በውስጡ ያነገበውን መርህዎ ነው። ይህንን ስል በእርግጥ ትዝብት ውስጥ እንደሚከተኝ በመገንዘብ ነው። ምክንያቱም እኔም እንደሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ የነአቶ ስዬን ወደ አንድነት መቀላቀል አምርሬ እቃወም ስለነበረ ነው። እቃወምም የነበረው እንደዚህ አይነቱ ነገር በውስጠ ደንቡ ውስጥ መካተቱን ካለመገንዘቤ የተነሳ ነው። በስተሁዋላ ብረዳውም እዬ አይነቱ አካሄድ በድርጅቱ መርህዎ እስከተካተተ ድረስ መደገፍ የግድ ይለኛል። በውሳኔው እንደኔ ያልተስማሙ ካሉ ያላቸው እድል ውሳኔውን መቀበል ወይንም የድርጅቱ ህግና ደንብ እንዲለወጥ መታገል ነው። ነገር ግን በክብርት ብርቱካን ሚደቅሳ እና በሌሎች የአንድነት ሰዎች የረቀቀውን ህገ ደንብ እንደግፋለን የምንል ከሆነ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ውሳኔውን መደገፍ ያለብን መስሎ ነው ለኔ የሚሰማኝ። ቢሆንም ቅሉ አሁንም ቢሆን በግሌ ውዥንብሬ እንዲጠራ እና የተነሱበት አላማ ከግብ እንዲደርስ አቶ ስዬ ከኢትዮያ ሕዝብ ይቅርታን መጠየቅ እንዳለባቸው አምናለሁ። አለበለዚያ ግን ጉዳዩ በአብዛኛው ኢትዮጵያውያኖች ዘንድ በጥርጣሬ እንዲታይ ያደርገዋል።*

### *የነ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እና አቶ ስዬ አብርሀ ወደ አንድነት መምጣት ጠቀሜታው ምን ሊሆን ይችላል?*

ዛሬ ገዢው መደብ ደጋፊዎቹን በሚያወናብድበት ስልቱ በመታገዝ እነኚህ ተቃዋሚዎች የድሮውን ስርአት ሊያመጡብህ ነው። ስልጣን ከያዙ ይፈጁሀል ወዘተርፈ የመሳሰሉትን አባባሎች በመጠቀም የሚያወናብድበት ስልቱ በከፊልም ቢሆን ይመክናል የሚል ግምት አለኝ። እውነት ለመናገር ደጋፊዎቹም እንደዚህ አይነቱ አባባል ቀልድ መሆኑን ሳይረዱት ቀርተው ነው? ወይንስ አውቆ የተኛን ሰው ቢቀሰቅሱት አይሰማም ነገር ሆኖባቸው ነው? ብቻ እንደዚህ አይነቱን ጥያቄ እንድጠይቅ የገፋፋኝ ነገር ቢኖር የትኛው ኢትዮጵያዊ ነው ሌላኛውን ኢትዮጵያዊ የሚፈጀው? እውነት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደለማኝ ቆሎ በደም እንደተሳሰረ ሳያቁት ቀርተው ነው? ብቻ ደጋፊዎቻቸው ያልተረዱት ነገር ቢኖር የነሱ ጠላት የሚደግፉት ድርጅት ብቻ መሆኑን ነው።

ወደ ዋናው ፍሬ ሀሳብ ስመጣ የነ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ወደ አንድነት መምጣት በወያኔ ስርአት ውስጥ ከፍተኛ አመራር ላይ ሆኖ ነገር ግን በወያኔ-ኢህአዴግ አምባገነን አመራር ለተማረረ እና መሄጃ አጥቶ ግራ ለተጋባው ኢትዮጵያዊ ወገን በር ከፋች ነው። ሌላው ደግሞ አይኗ እየጠፋ ያለችውን ኢትዮጵያ ጭራሽኑ ከመጥፋቱ በፊት ሊያድናት ይችላል የሚል ግምት አለኝ። በአስራ ስምንቱ የወያኔ አገዛዝ ስርአት ውስጥም በኢትዮጵያውያኖች መሀል የከፈተውን ውዥንብርም ያጠራዋል። በጥቅሉ በኢትዮጵያውያኖች መሀል አንድነትን የበለጠ ይፈጥራል። ያስተሳስራል።

ይህ እንዳለ ሆኖ የምዕራብ አገሮችም የኢትዮጵያውያኖችን መከፋፈል አጋጣሚ ተጠቅመው ደካማዋን ኢትዮጵያ አግኝተው ለመቀራመት አኮብኩበው ያሉበትን ሁኔታ ያመክነዋል የሚል ግምትም አለኝ። በመሰረቱ የምእራብ አገሮች የእጅ አዙር አገዛዙን እያጧጧፉት ነው። እዬም ዘመናዊ ቅኝ አገዛዙ እየሰፋ ሄዶ ከማንወጣበት ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት ለኢትዮጵያችን ስንል ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያይዝን ልንታገለው ይገባናል።

እና ነገሮችን ከዚህ አንጻራዊ ሁኔታዎች ጋ ስናያቸው አንድነት የወሰደው ጠንካራ ውሳኔ እና አቋም ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን ሁኔታ የዳሰሰ ይመስላል። እንግዲህ ነገሮችን በቀናነት ካየናቸው እና ይቅር የመባባልን ባህል እያዳበርን መጓዝ ከቻልን ችግራችንን በፍጥነት ልንቀርፈው እንችላለን። የህዝባችንንም የመከራ ዘመን ልናሳጥረው እንችላለን። አገራችንንም እኛ የምንሰደድባት ሳይሆን ሌሎች የአገራችንን ብልፅግና ሰምተው ወደኛ የሚሰደዱባት አገር ልንፈጥር እንችላለን።

### *አንድነት እንደ ድርጅት የሚያገኘው ጠቀሜታ*

አንድነት ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ ልትቋቋመው የምትችለውን ሁኔታ በጥንቃቄ አጥንተው ከዚህ ውሳኔ ላይ መድረሳቸው ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ተስፋ ሰጪ ነው። ምክንያቱም አብዛኛው በገዢው መደብ ውስጥ ወንጀል የሰራ ሰው ነገር ግን በሰራው ወንጀል ተፀፅቶ እያም ፀፀት አላስቆም አላስቀምጥ ያለው እና ፀፀቱም ቢሰማው መሄጃ ከማጣት የተነሳ ወደሌላ ወንጀል እየተሸጋገረ ለሚኖር ሰው ከወንጀሉ ታቅቦ ወደ ተቀደሰ መንገድ እንዲሄድ ጥሩ አመላካች መንገድ ነው።

እና ወደማጠቃለያው ስመጣ አንድነት ወደፊት ከሚያሳያቸው ስራዎቹ ጋ ተደምረው ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ድርጅት ሊሆን ይችላል። ከገዢው መደብ በሚወጡ ባለስልጣኖችም ሆነ ደጋፊዎች ከፍተኛ ድጋፍን ሊያገኝ ይችላል። በአብዛኛው ኢትዮጵያውያንም ከፍተኛ ድጋፍን ይጎናፀፋል። ወደፊት ለምትመሰረተው ኢትዮጵያም በፖለቲካው መስክ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል። ለአገራችን ጠንካራ ተቃቃሚም ሆኖ መቀጠል ይችላል።

በመጨረሻም ለፅሁፉ ግድፈት ይቅርታ እየጠየኩኝ ለዛሬ በዚህ እሰናበታለሁኝ።
**አምላክ ኢትዮጵያን ይጠብቅ**

ሕዝቅያስ ፍቅሬ(ከኬኔክትኬት/አሜሪካ)
AGERE_ETHIOPIAA@yahoo.com